Title: Kase Gosa, Ejegu Sherberu, Denberu Mamo,Demesew Tulula, and Tadese Alemu Interview

Creators: Gosa, Kase; Ejegu, Sheberu; Mamo, Denberu; Demesew, Tulula; Alemu, Tadese; Taye, Hiwot; Bekele, Getnet

Date: June 3, 2009

City: Tullure

Country: Ethiopia

Afircan Oral Narratives: aodl.org/oralnarratives

እኔ ፕሮፌሰር ጌትነት በቀለ እባላለሁ፡ የመጣሁት ከአሜሪካን ሀገር ነው ዓለም ባንክ ኦክላንደና ሚሺጋን ዩኒቨርስቲዎች ጋር በማሆን አንድ ጥናት ለሞድረግ ነው የጥናታችን ዋና ዓላማ ስለ የአየር ሁኔታ (Enviroment) ያለበትን ሁኔታ ለማጥናት ሲሆን በተለያየ ሳይንሳዊ መንገድ የሚደረገው ጥናት የአካባቢወን ነዋሪዎች /ገበሬዎች/ ያካተተ ባለማሆኑ ብዙም መፍትሔ ስላላመጣ የአካባቢው ነዋሪዎች የገበሬዎቹ ሃሳብ የሚፈልጉት ምንድነው የሚለወን ይዘን በተለያየ ቦታ ጥናት እያደረግን ነው የጥናታችንም ዋና ዓላማ አካባቢያችን እንዴት ነው የምናሻሽለው ዝናቡ ለምንድነው የሚጠፋው ሜቴ ምን እየሆነ ነው እንዴት ተለወጠ የሚለው ላይ ለማጋገር ነው በተለይ የድሮወን የምታወቁትን እስከምታወቁት ድረስ የሰማችሁትንም ቢሆን እንድትገልፁልኝ እፈልጋለሁ፡

እራሳችሁን ካስተዋወቃችሁኝ በኋላ ቀጥታ ወደ ጥያቄና ሜልስ እንገባለን፡፡

1. አቶ ጎሣ ካሣዬ እባላለሁ የተወለድኩት እዚሁ ቀበሌ ወስጥ ነው በግብርና ነው ቱሉ ወረዳ ነው፡
2. አቶ ታፈረ ጎዴ አባላለሁ ትወልዴ እዚሁ ነው የምትዳደረወም በግብርና ነው
3. አቶ እጅጉ ሽብሩ አባላለሁ ዕድሜ 53 እዚሁ ተወልጄ እዚሁ ነው የምነራው
4. አቶ ድንበሩ ማሞ ዕድሜ 43 ስራ ግብርና
5. አቶ አበበ ዝናብ እዚሁ ተወልጄ ዕድሜ 32 ተማሪ ነበርኩ አሁን የምተዳደረው በግብርና ነው
6. አቶ ደምሳቸው ግርማይ ትወልዴ እዚሁ ነው ዕድሜ 33 በ1987 ትምህርቴን ጨርሼ ነው ወደ ግብርና የገባሁት የህብረት ሥራ ማህበር የሂሳብ ሥራ እሠራለሁ፡

7. ወ/ሮ ህይወት ሀይሌ የግብርና ባለሙያ ነኝ ግብርናን ወክዬ ነው እዚህ የተገኘሁት

ጥ. ሁላችሁም እዚህ ያላችሁት የምታርሱበት የራሳችሁ የሆነ መሬት አላችሁ?

መ. የሌለንም አለን በኮንትራት እንሠራለን

ጥ. የሌላችሁ ሰዎች ለምን መሬት እንደሌላችሁ ብታስረዱኝ

መ. እኔ መሬት በሚከፋፈልበት ጊዜ አልደረስኩም አልተወለድኩም አባቴ ከራሱ መሬት ላይ አንድ ቀርጥ መሬት ሰጥቶኝ በሱ ነው የምተዳደረው በተጨማሪም እየገዛሁኝ ነው የማርሰው

ጥ. እየገዛሁ ስትል እንዴት ነው?

ጥ. በኮንትራት እየያዝኩኝ ማለቴ ነው

ጥ. ገበሬ ማህበር መሬት አይሰጥም እንዴ?

መ. መሬት የለም ስለዚህ አይሰጥም

ጥ. ሌላ መሬት የሌለው አለ ማን ነው?

መ. መሬት የሌለን ወጣቶቹ ነን

ጥ. ወጣቶቱ መሬት ከሌላቸው ወደፊት ምን የሚሻል ይመስላችኋል? ለወጣቶቹ ምን ተስፋ አላቸው ሌላ ስራ መፈለግ ነው ያለባቸው ወይንስ ምን እስኪ እዚህ ላይ አስተያየታችሁን ብትሰጡኝ?

መ. ወደፊት መሬት የማግኘቱ ሁኔታ ተስፋ የለውም በህብረት ተደራጅተው አንዳንድ ሥራዎችን ማስራት እንጂ መሬት ከእንግዲህ ወዲያ እየጠበበ እንጂ ስለማይሰፋ ከብት እርባታ ዶሮ እርባታ የመሳሰሉትን ስራዎች ነው ማስራት ያለባቸው

ጥ. ሌላ ተጨማሪ አስተያየት ያለው ካለ በዚህ ሃሳብ ላይ?

መ. በአሸዋ ላይ ለምሳሌ በወንዝ አካባቢ ወጣቱ ተደራጅቶ በአሁኑ ሰዓት አሸዋ በማምረት እየሠሩ አሉ ይህንን ማስራት ይችላሉ እንዲሁም የድንጋይ ካባ ባለበት አካባቢ በመደራጀት ማውጣት ይችላሉ፣

እንዲሁም ዶሮ እርባታ የማሰለወን ሥራ ማንግስትም ድጎማ እያደረገ ስለሆነ በዚህ ሜሎኩ መተዳደር ይችላሉ፡፡

ጥ. እንግዲህ አሁን ለወጣቶቹ ከእርሻ ሥራ ይልቅ ተስፋቸው በሌላ ሥራ ማስክ ነው ማለት ነው?

መ. አዎ ትልቁ ነገር ሜሬት ከደርግ ጊዜ ጀምሮ የተለካበት ነገር የለም ያለው እዛው በነበረበት ሥርዓት ነው የእርሻ ሜሬትም ያለው ጠበብ ነው አንድ ገበሬ ያለው ቢበዛ ከአንድ ሄክታር እስከ ሶስት ሄክታር ብቻ ነው

ጥ. ከሶስት ሄክታር በላይ ያለው የለም?

መ. የለም ስለዚህ አባት ለልጁ ካለው ሶስት ሄክታር ላይ አንድ ቀርጥ ይቆርጥለታል ያችን በማከዛትና ከሌላው ኮንትራት በማያዝ ይጠቀሜል /ይተዳደራል/ ምንም ከሌለው ደግሞ ያው ቅድም እንደተገለፀው በሜደራጀት ነው የሚኖሩት መንግስትም ሁኔታወን ያመቻቻል፡፡

ጥ. አንድ ቀርጥ ማለት ስንት ነው?

መ. ሃምሳ ሜትር በሃምሳ ነው

ጥ. ስለሜሬት ማካፋፈል አንስታችሁ ነበርና እስሲ ስለሱ ትንሽ እንነጋገርበት በደርግ ጊዜ ነው ሜሬት ማካፋፈል የተጀሜረወና ከዛ በፊት ስላለው እንነጋገራለን ደርግ በገበሬ ማህበር ሜሬት ማከፋፈሉ ጥሩ ነው ትላላችሁ? ወይስ ጥሩ አይደለም? ከዚህ የተሻለ አማራጭም ካለ ሃሳባችሁን ስጡ?

መ. ደርግ ሳይመጣ ትንሽ ሰዎች ነበሩ ሜሬት ይዘው ቁጭ ብለው የነበሩት በዛን ጊዜ ሌላው ጭሰኛና ተበዳይ ነበር ደርግ ሲመጣ ሜሬት ለሁሉም ሰጠ ሁሉም ባለ ሜሬት ሆነ ምርትም ከዛ ወዲህ ነው ማምረት የተጀሜረው የሌለወም በአሸዋ እየተደራጀና ሜሬት እየተኮናተረ ይሠራ ነበር ደርግ ባይመጣ ኖሮ ትንሽ ሰው ነበር ሜሬት ይዞ የነበረው ለቀበሉ ብቻ ነበር ሠርቶ የሜኖረው

ጥ. ትንሽ ሰው ነበር ሜሬት የያዘው ብለወኛል እነሱ እነማን ናቸው?

መ. በአሁኑ ሰዓት እነሱ የሉም ሁሉም አልፈዋል

ጥ. ሌላው ገበሬ እንደጠሰኛ ሆኖ ነበር የሚያገለግለው ማለት ነው አንዳንዶቹን በህይወት ባይኖሩም ስማቸወን አታስታወሱም?

መ. ማሜ ደስታ የፀሐፊ ትዕዛዝ ሜሬት የሜልከኛ ይባላል፡፡

ጥ. ሜልከኛ የሚባሉት እነማን ናቸው?

መ. ሜልከኛ የሚባሉት እዚህ አካባቢ ተሊላ በዳዳ የሚባሉ ነበሩ

ጥ. ብዙ ሜሬት ነበራቸው?

መ. አዎ ብዙ ሜሬት ነበራቸው አንድ ሰው ነው ይዞ የነበረው

ጥ. በደርግ ጊዜ አንድ ሰው ይዞት የነበረውን ነው የተከፋፈለው?

መ. አዎ አንድ ሰው ይዞት የነበረውን ብዙ ሰው ይጠቀምበታል ማለት ነው

ጥ. ከደርግ በፊት ስላለው ሁኔታ የምታውቁት አላችሁ? በእርግጥ አንዳንዶቹ ትንንሾች ናችሁ ለምሳሌ የባላባት ሜሬት የሚባል ነበር?

መ. ባላባቶች የሉም

ጥ. በእርሻው የምትዘሩት አዝርዕት አይነት ምን ያህል ተቀያይሯል? ወይስ አንድ ዓይነት ነው የምትዘሩት አሁንስ በብዛት ምንድነው የምታመርቱት?

መ. አሁን ምርጥ ዘር ነው የምንዘራው ድሮ ያራንዳቶ የሚባል ስንዴ ነበር የምንዘራው እሱ ጠፍቷል ጨርሶ የለም አሁን ምርጥ ዘር ነው የምንዘራው

ጥ. ድሮ የሚሉት መቼ ነው በደርግ ነው?

መ. በአፄ ኃ/ስላሴ ጊዜ ነው በዛን ጊዜ ያራዳቶ ስንዴንና ትንሽ ጤፍ ነው የምንዘራው

ጥ. በብዛት ሰንዴ ነበር የምትዘሩት?

መ. አዎ በብዛት የምንዘራው ያራንዳቶ የሚባለውን ስንዴ ነበር ጤፍ በትንሽ እንዘራ ነበር ማዳበሪያ በዛን ጊዜ አልነበረም ማዳበሪያ መግባት የጀመረው ቆይቶ ነው አሁን ግን ምርጥ ዘር ነው የምንዘራው

ጥ. ምርጥ ዘሩ የስንዴ ብቻ ነው? ጤፍና ሌሎቹስ?

መ. የጠፍ የለም ስንዴ፥ ሽንብራ፥ ነው የምናገኘው ጠፍ ዘንድሮ ይጀምራል ተብሏል፡፡

ጥ. ቅድም መሬት አንሶናል እየተኮናተርን ነው እምናርሰው ያሉ ሰዎችን አናግሬ ነበር መሬት አንዴት አገኛችሁ ከቤተሰብ ነው? ወይንስ ከገበሬ ማህበር ይህንን ብትገልፁልኝ? አሁን አንተ ወጣት ነህ እንዴት አገኘህ?

መ. እኔ ያው ቅድም እነሱ እንደተናገሩት በደርግ ጊዜ ልጅ ነበርኩኝ ቤተሰቤም ደካማ ነበሩ በደርግ ወቅት የዘማች እርሻ አለ የህብረት እርሻ አለ በቤተሰብ ስር እኔ ተወክዬ ማህበር ብገባ ቤተሰብ የሚኬከው ሰው የለም ግድ የቤተሰብ መሬት ይወሰዳል በማህበርና በዘማች እርሻ ካለተሳተፉ መንግስት መሬት ይወስዳል ገበሬ ማህበር ለመግባት ዕድሉን አላገኘሁም ተልኬና ጦሬ ነው የቤተሰብ መሬት የያዝኩት

ጥ. ሌሎችስ እንዴት እንዳገኛችሁ ብትገልፁልኝ?

መ. አሁን መሬት በዛን ጊዜ 18 ዓመት ከሞላ እናትና አባት መሞላቱን አረጋግጠው ነው  መሬት የሚሰጠን የሚሰጠው መሬት ሁለት ቀርጥ ተክል ነው ከዛ በላይ የለም ከዛ ደግሞ አንድ ቤተሰብ ካለኝ ተክል ይጨመራል እኔ እንደዚህ ነው ያገኘሁት

ጥ. እርስዎ የማን መሬት ተሰጦዎት?

መ. የመንግስት መሬት ነው የተሰጠኝ አባቶቻችን የላቸውም እኛ የሰው ነበር የምናርሰው

ጥ. እርስዎ ያን ጊዜ የተሰጦዎት መሬት ከዛ በፊት ያልታረሰ መሬት ነው ወይንስ ሌላ ሰው ያረሰው

መ. ያልታረሰም አለ የታረሰም አለ?

ጥ. ስለ ድሮ ብጠይቃችሁ ታውቃላችሁ ለምሳሌ በአፄ ምኒልክ ዘመን እንዴት አንደነበር የሰማችሁት ካለ ስለ አስተራረሳቸው?

መ. እኛ የሰማነው ታሪክ የለም

ጥ. አንዳንድ ሚጃዎች በድሮ ጊዜ በዚህ አካባቢ የከብት አርባታ በጣም የተስፋፋ እንደነበርና የእርሻ ስራ ከማስራት ይልቅ ገበሬዎቹ ከብት ማርባት ይፈልጉ እንደነበር ይባላል ይህን የሚያውቀው አለ?

መ. ይሄ ትክክል ነው እኔም በእረኝነትም ቢሆን ትንሽ ደርሼበታለሁ፡፡ ያኔ የነበረው ከብት ብዛት በጣም ብዙ ነበር በጥራትም አሁን ካለው ጋር በምንም አይገናኝም ያኔ በጣም ጥሩ ምኩቱ ነበር ያለው አሁን ግን ከብቱ እራሱ ማገዶ ነው፡፡

ጥ. ይሄ ችግር ታዲያ ከምን የመጣ ይመስላችኋል?

መ. አሁን ቤተሰባችን ሰፊ ነው እነሱን ለማስተዳደር ለማገዶ ደን እየተጨፈጨፈ እርሻ እየበዛ የግጦሽ ሜዳ እየጠፋ ነው የመጣው

ጥ. የግጦሽ ሜዳቱ እየታረሰ ከሄደ ያለው አማራጭ ከብት መቀነስ ነው ማለት ነው?

መ. አዎ በዚህ ምክንያት ነው አማራጭ የለም

ጥ. እርስዎ ደርሰውበታል በትክክል ከብት በነበረበት ጊዜ

መ. አዎ በትክክል ደርሼበታለሁ እረኝ ነኝ በአፄ ኃ/ስላሴ ዘመን ነው አሁን የተገለፀው ሁሉ ትክክል ነው የድሮና የአሁን ከብት ምንም አይገናኝም ድሮ አንድ ወይፈን ሲወለድ በ3 ዓመት ነው የሚያርሰው ዛሬ ግን በ10 ዓመት አያርስም የሚበላ ነገር የለም ሜዳት የለም ሁሉም ቤተሰብ አለው ከብት የሚባላው ያችኑ ያረሳትን ገለባ ብቻ ነው እንጂ ሣር የለም የድሮ ከብት ሣር ይበላል፡፡ የድሮ ፍየል ቅጠል አለ ቅጠል ይበላል፡፡

ጥ. በአፄ ኃ/ስላሴ ጊዜ ሜዳት በጥቂት ባለሀብቶች እጅ የተያዘ ነበር ብላችኋል፡፡ እነርሱ እንግዲህ የዛን ጊዜ የራሳቸውን ጭሰኛ አምጥተው ነበር የሚያሳርሱት ይባላል በዛን ወቅት የሰው ጉልበት ባለማኘቱ ይሆን እርሻውን ትተው ወደ ከብት እርባት የገቡት?

መ. በዛን ወቅት ሰው ለእነሱ ግብርና ነው የሚያገለግለው ደርግ ሜዳት ካከፋፈለው በኋላ ነው ለራሱ የሠራው

ጥ. ጭሰኞች ግብር የሚገብሩት ምን ያህል ነበር?

መ. እኩል የሚያርሱ ሲሶም የሚያርሱ አሉ እንደዚህ ነበር

ጥ. በጣሊያን ዘመን እዚህ አካባቢ ጣሊያኖች ያደረጉት ነገር አለ? ሌላ አካባቢ ሳነጋግር ደብረዘይት አካባቢ በጣሊያን ጊዜ /ዘመን/ እርሻ ሁሉ በእነርሱ ምክንያት ነው የተስፋፋው ብለዋል የምታውቂት አለ ?

መ. ምንም የምናውቀው የለም አብዛኞቻችን ልጆች ነን፡፡ መንገድና ድልድይ ሰሩ ሲባል እንጂ እርሻ አረሱ የሚባውን አልሰማንም

ጥ. ለምንድነው የምታርሱት?

መ. ለምንበላው ነው

ጥ. መጀመሪያ እርስዎ ወደ እርሻ ሲሄዱ የምባላውን ልረስ ብለው ነው የሚሄዱት?

መ. ሌሊት ስተኛ አስባለሁ ቀለብ ምን እንደሚሆን ልጆቼን አስባለሁ ይሄ ሜዳ ማልበጥ አለበት ብዬ ማወቅ አለብኝ ያን ካረኩ በኋላ ወደ እርሻ እገባለሁ፡፡

ጥ. በመጀመሪያ እርስዎ እርሻ ሲያርሱ የሚያስቡት ቤተሰቤን ምን አበላለሁ የሚለውን ነው

መ. አዎ እሱን ነው የማስበው

ጥ. አርሼ ሸጬ ገበያ ሞጀ፣ አዲስ አበባ ይሄ ይፈለጋል የሚለውን አስበው አያውቁም?

መ. ይሄንን የማስበው በሁለተኛ ደረጃ ነው ዋናው የምናመርተው ለቤተሰብ ነው መጀመሪያ ራሳችንን አድነን ነው ወደ ገበያ የምናስበው ዛሬ የሚርሰው ለቀለብ ለቤተሰብ ልብስ ለትምህርት ቤት የሚለውን እናስባለን በተራ

ጥ. እዚህ አካባቢ አብዛኞቻችሁ የምትመግቡት ምንድነው ለምሳሌ አሁን ምሳ ምን ትበላላችሁ?

መ. እንጀራ በሽሮ

ጥ. ይሄ ምግባችሁ ከቤት ያመረታችሁት እንጂ ገዝታችሁ አይደለም?

መ. አዎ አንገዛም ከቤት የተመረተ ነው፡፡ አልፎ አልፎ የምንገዛው ይኖራል ዘንድሮ ግን አምርተን ለማዳበሪያ ዕዳ ለመክፈል ነው የተዘጋጀነው ለቀለብ ከብትም ቢሆን እንሸጣለን፡፡

ጥ. ከምታመርቱት ምርት ምን ያህሉን በዓመት የምትሸጡ ይመስላችኋል?

መ. ብዙ ነው የምንሸጠው

ጥ. በግምት 10 ኩንታል አንድ ገበሬ ቢያመርት ምን ያህሉን ይሸጣል

መ. የማዳበሪያ ዕዳ ካለበት ማሎውን ሸጦ ይከፍልና ከብት ሸጦ ቀለብ ይገዛል

ጥ. ከገበያ ጋር ያላችሁ ግንኙነት ከፍ ያለ ነው ማለት ነው?

መ. አዎ ለምሳሌ የተወሰነውን ለራሳችን የተወሰነውን ለገበያ እናደርጋለን

ጥ. ብዙ ጊዜ የት ነው የምትሸጡት?

መ. ሞጆ ወስደን ከተማ ነው የምንሸጠው

ጥ. እዚህ ድረስ መጥቶ የሚገዛችሁ ነጋዴ የለም ?

መ. የለም አንዳንድ ጊዜ አገልግሎት ይገዛል እሱ ወዲያው ገንዘብ አጥቶ ይቆማል ስለዚህ ገበያ ወስደን ተንገላተን ነው የምንሸጠው

ጥ. በምንድነው የምታጓጉዙት እህሉን?

መ. በአህያ

ጥ. አንዳንዶቻችሁ በአሁኑ ወቅት የገበሬው ችግር ምንድነው ዋና የምትሉትን አንድ ንገሩኝ ሶስት አራት ሳይሆን ብትባሉ ምንድነው የምርመርጡት

መ. ዋና ችግራችን ማዳበሪያ ነው በፊት የሚሰጠን በብድር መልክ ነበር አሁን ግን ገዝተን ነው የምንጠቀም በብድርም ብንወስድ ከብት ሸጠን የታረሰ መሬት ሸጠን ነው የምንከፍለው አሁን የምናመርተው ምርትም ጥራጥሬ ነው ጤፍ ማዘራት አይቻልም የሚዘራባቸው የተወሰኑ ናቸው ማዳበሪያ የማይፈልጉ ቦሎቄ፣ ባቄላ አተር ነው ዋናው ችግራችን ማዳበሪያ ነው፡፡

ጥ. የማዳበሪያ ዋጋ ከፍተኛ መሆን ነው ወይንስ ማጣት?

መ. ዋናው ዋጋው መኖሩ ነው አብላጫው በኛ ሚከል ያሉት ወጣቶች ናቸው ስለዚህ መሬት የላቸውም የሚኖሩት ተከራይተው ነው ለመሬት ያወጣሉ፣ የማዳበሪያ ዋጋ በመኖሩ ምክንያት የተኮናተሩትን መሬት ማለሰው ይሸጣሉ፡፡

ጥ. ሁላችሁም በዚህ ሃሳብ ትስማማላችሁ?

መ. አዎ ልክ ነው እንስማማለን ቀደም ሲል ማዳበሪያ ልምድ ነበረው በአንድ ጊዜ ትተህ ወጣ ሲባል ሁሉም ገበሬ ነው የተቸገረው እንኳንስ ማዳበሪያ ሚሉ በሚሉ ገዝቶ ሊዘራ ቀርቶ ከቤቱ አንድ ቡናና 5 ኪሎ እህል ይዞ የሚይወጣ ገበሬ አለ ቀደም ሲል ምርጥ ዘር በብድር ነበር አሁን እነሱ ሁሉ ቀሩ አሁን የስንዴ ምርጥ ዘር መጥቶ ነበር ግን ለመውሰድ ፈቃደኛ ብንሆንም በምን አቅሙ ይወሰድ ገበሬው ማዳበሪያ ግዢ ምርጥ ዘር ግዢ ሲሆን ገበሬው የሚዛበት አቅም የለውም

ጥ. ማዳበሪያ በብድር ትወስደላችሁ?

መ. በፊት እንወስድ ነበር አሁን ሚሉ በሚሉ ግዢ ነው

ጥ. መቼ ነው እዚህ አካባቢ በብዛት ማዳበሪያ ማጠቀም የጀመራችሁት?

መ. የጀመርነው በአፄ ኃ/ስላሴ ነው በደንብ ግን ማጠቀም የተጀመረው በ1969 ነው፡፡ በማህበር እየተደረገ ነው የተጀመረው

ጥ. ለምን ማዳበሪያ ትጠቀማላችሁ የድሮ ገበሬዎች አይጠቀሙም ለምን ይመስላችኋል?

መ. ያኔ ህዝቡ ትንሽ ነበር አሁን ህዝብ ጨምሯል በፊት በ6 ሰው የተያዘው ጋሻ አሁን ያ መሬት 80 ሰው ነው የያዘው ያኔ መሬቱ ብዙም አልታረሰም ስለዚህ መሬቱ ማዳበሪያ አላስፈለገውም አሁን ግን ህዝብ ስለበዛ ሁሉም ተመንጥሮ ስለታረሰ ለምነቱን ስላጣ ነው ማዳበሪያ ያስፈለገው፡፡ በፊት ጓያ ሽምብራ ነበር የሚዘራው አሁን የሚዘራው ጤፍ ነው፡፡

ጥ. ከሌላው ጊዜ በበለጠ ለምን ነው አሁን ጤፍ የሚዘራው?

መ. ጤፍ የሚዘራው ገቢ ስለሚገኝበት ነው ሁሉንም አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ማሟላት የሚቻለው ጤፍ ተሸጦ ነው ጤፍ ዛሬ አንድ ሺ ብር ሲሆን ስንዴ 400 ወይም 450 ነው ይህንን ሸጠህ ማሟላት የምትፈልገውን ማሟላት አትችልም ጤፍ ከሸጥክ ግን ትቋቋማለህ፡፡

ጥ. የአየር ንብረት ማዛባት እየተፈጠረ ነው ይባላል እናንተ ያስተዋላችሁት ነገሮች አሉ የዝናብ ማዛባት የመጥቅ ወይም የመቀዝቀዝ ነገር ልብ ያላችሁት አለ?

መ. አዎ የዛሬ 7 ዓመት ቀደም ቀደም አድርገን ዘራን ዝናቡ ወዲያው በአበባ አቋረጠ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ጤዛ ይጥልና ከጣለ በኋላ ቀይ ነገር አለ ዋግ ይጥላል ማለት ነው፡፡ የአየር ሁኔታው በጣም ጥሩ አይደለም እየፈራን ነው ለጥራጥሬ ነው እንጂ ጤፍ ቢዘራ ይወጣዋል፡፡ የሚጥለውም ዝናብ አጥጋቢ አይደለም በዚሁ ከዘለቀ በተለይ ለጤፍ አይመችም በጣም ያሰጋል፡፡

ጥ. ቅድም ስጠይቅ ዋናው ችግራችን ማዳበሪ ነው ብላችሁ ነበር በበሽታስ በኩል የሰው፣ የከብትም ሆነ አዝርዕትም ላይ የመጣ በሽታ ወይም እንደወረርሽኝ ያለ ነገር ተምቾ ሊሆን ይችላል የተከሰተበት ጊዜ አለ በእናንተ ዘመን?

መ. እዚህ አካባቢ ባጋጣሚ ወቅቱ ትዝ አይለኝም እንጂ ጤፍ ዘርቼ ተምቾ እንዳለ ወሮት መድሀኒትም በረጭ ወደ ሌላ እየተሳበ አበላሽቷል፡፡ ከዛ ወዲህ ግን አላጋጠመኝም፡፡ ጤፍ ዝርዝር ላይ ህዳርና ታህሳስ አካባቢ ፌንጣ ይመጣል እሱ ብዙ ጊዜ ያጋጥማል፡፡

ተባይ ተለይቶን አያውቅም ሽምብራ፣ ምስር እና በተለይ አተር ላይ በጣም ያጠቃዋል መድሀኒት ከነጋዴዎች እየገዛን የልማት ሠራተኞችም እየተባበሩን መድሀኒት እየረጨን ነው እንጂ ተለይቶን አያውቅም ሽምብራና ጥራጥሬ ይዘራል እንጂ ብዙ ፍሬ አይገኝበትም፡፡

ጥ. መድሀኒት ለመግዛት ብዙ ወጪ ታወጣላችሁ?

መ. አዎ በአመት አንድ ሰው እስከ ሁለት ሊትር ይገዛል አንዱ ሊትር 200 ብር ሂሳብ ነው ስለዚህ ይወጣል፡፡

ጥ. ይሄ ከማዳበሪያ ወጪጋር ሲደመር ይበዛባችኋል ማለት ነው?

መ. አዎ ባለፈው ሽምብራ፣ ባቄላ፣ አተር፣ ምስር ሲያብብ ስለማቋረጥፈው የግድ መድሀኒት ያስፈልጋል መድሀኒቱን ከግል ነጋዴዎች እንገዛለን ጥሩ ነው ይላሉ ግን ጥቅም ሳይሰጥ ይቀራል እህሉንም ሊጎዳ ይችላል፡፡ ኪሳራ ያስከትላል፡፡

ጥ. በግብርና ሚኒስቴር በኩል እነዚህ መድሀኒቶች አይቀርቡም?

መ. ማሱ በማሱ አይገኝም  አይቆጣጠሩትም ከዛ የምናገኘው ደግሞ ተባዩን አይፈጀውም ከግል የምንገዛው ይሻላል፡፡

ጥ. ስለ ደን ሁኔታው እንዴት ነው እዚህ አካባቢ ደን ድሮ ነበር? ወይንስ አሁን? ያለ በጠቅላላ ብታስረዱኝ

መ. ደን ድሮ ታች ታቹን በማሱ ጫካ ነው መተላለፊያ አልነበረም የተለያየ አይነት በእኔ ዕድሜ አሁን ግን አንድ እንጨት አይታይም ድሮ አጥር ለማጠር ወጣ ብለን ቆርጠን መጥተን ነበር አሁን ግን ምንም የለም ያው የሚታይ ነው፡፡

ጥ. በዚህ ላይ ተጨማሪ ካለ

መ. ስለ ደን ጉዳይ ከተነሳ ህዝባችን በከብት ነበር የሚተዳደረው የሚለው ትክክል ነው ጤፍ ለምንድነው የሚዘራው የሚለው ለከብትም ምግብነት ጭምር ነው ከሜሬት ጥበት የተነሳ ደኑ እየተመነጠረ ወደ እርሻ ተገብቷል የግዴታ ከዓመት ዓመት ተመንጥሮ ወደ እርሻ ተገብቷል፡፡ አሁን ለማገዶ እንኳን ሁሉም በደጁ ባህር ዛፍ እየተከለ ነው የሚጠቀመው

ጥ. ስለዚህ ከብቶችና ዛፎች በአንድ አካባቢ ነው የጠፉት ማለት ነው?

መ. አዎ

ጥ. እርሻ ሲጀመር እዚህ አካባቢ የከብት ፍግ ትጠቀሙ ነበር?

መ. አዎ ይደረግ ነበር ግን አሁን እንጨትም ስለጠፋ ሰው ኩበት አድርጎ ለማገዶ ሰለሚጠቀምበት ፍግ ብዙ አይገኝም፡፡ ገበሬ ከምፖርስ ማስራት አላወቀበትም እንጂ ከአጠፋሪስ ከአራሙቻ ኮምፖስ ማስራት ይቻላል፡፡ ከብት የማገሱ ነገር እውነት ነው ግን ከቅጠልም ይሰራል ከምፖስ ግን ገበሬው ዕውቀት የለወም እኔ ይህንን ያወቅኩት ሰልጥኜ ነው፡፡

ጥ. ገበሬዎች ከከብት ፍግ ማዳበሪያ እንደሚገኝና የተሻለ ምርት እንደሚገኝ ያወቃሉ?

መ. አዎ ያወቃሉ ግን አይጠቀሙበትም አሁን እያንዳንዱ ቤት ብንሄድ ይገኛል ግን አይጠቀሙበትም

ጥ. ሜሬት አለን ያላችሁ ሰዎች ሜሬታችሁን ማሻጥ ማለወጥ እሱን አስይዞ ገንዘብ ማበደር ትችላላችሁ?

መ. ማኮናተር እንችላለን ማሻጥ ግን አንችልም

ጥ. ሜሄት ማሻጥ በፈቀድ ጥሩ ይማስላችኋል? ወይስ መጥፎ?

መ. ሜሄት እንዴት ይሸጧል ማሻጥ የለበትም

ጥ. ለምን?

መ. ማሻጥ ቢቻል ለጊዜው ገንዘብ እናገኛለን ገንዘቡ ሲያልቅ ግን ተጎጂ እንሆናለን ሜሬቱም ከኔ አልፎ ቤተሰቤም ሊጠቀምበት ይችላል፡፡ ከተማ ጥሩ ሜሬት ነበራቸው ወደ መቶ መቶ ሃምሳ ሺ ብር ግምት አገኙ አሁን ግን ምንም የላቸውም

ጥ. ሌላ ማጠቃለያ ሃሳብ አላችሁ?

መ. ቅድም ሲያቀርቡ አንድ ያላችሁን ችግር ንገሩኝና እፈታለሁ ብለዋል ምናልባት ያንን የማዳበሪያ ችግር መቅረፍ እንኳን ባይቻል ማዳበሪያ ስንጠይቅ ኮምፖስት ተጠቀሙ ነው የምንባለው እና ሌላም ወሃ ችግር አለና ያንን ወሃ እንኳን ወደዚህ ለማቅረብ የሚቻልበት መንገድ ቢመቻች፡፡ እኔ 8 ልጆች ቢኖሩኝ 8 ቀረድ ሊኖረኝ ይችላል እነሱ ከሰኔ 30 እስከ መስከረም 2 ነው የሚኖሩት አረም የሚመጣው ከዛ በኋላ ነው እነርሱ ት/ቤት ይገባሉ መንግስት የተዘራው ሜሬት እንዳይበላሽ መድሀኒት አዘጋጅቷል ይህንን ባልና ሚስት አርሞ ስለሚይቻል ማዳበሪያ ቢመጣልን ይህንን ለማለት ነው፡፡

የማዳበሪያ ችግር የዚህ ሀገር ችግር ብቻ ሳይሆን በዓለም ላይ ያለ ችግር ነው ህንድ ለምሳሌ እንወሰድ ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር ያላት ናት አብዛኛውም ህዝብ በግብርና የሚተዳደር ሲሆን ማዳበሪያ ማጠቀም ከዛ ነው የተጀመረው እና አሁን የማዳበሪያ ዋጋ ሜጨመር እያሳሰበ የመጣ ነገር ነው ማዳበሪያን የሚቀርበው የዓለም ባንክ ነው የዓለም ባንክ ደግሞ አሁን እንዴት ልረዳ እችላለሁ እያለ እያሰበ ነው ይህም ጥናት ያስፈለገው፡፡

ችግራችሁን ለማወቅና የመፍትሔ ሃሳብ ለማምጣት ነው ስለዚህ ይህ የደረግነው ወይይት ይጠቅመናል ምን መደረግ አለበት የሚለውን ያመላከታል፡፡ እናንተ አሁን ማዳበሪያን እየፈለጋችሁ ነው አንዳንድ አካባቢ ደግሞ ይህንን ሜዳበሪያ አስቀሩልን ሜሬታችን ጉበ ለመደ ያሉ አሉ፡፡ ከእናንተ ግን ጠቅሞናል ትላላችሁ ስለዚህ በነዚህ ሃሳቦች ተነስተን ጠቃሚ ስራ እንሠራለን፡፡

በጣም አመሰግናለሁ ጊዜያችሁን ከኔ ጋር ስላጠፉችሁ ፡